የገቢዎች ሚኒስቴር

# የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 142/2011

የካቲት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No 1

በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በወቅቱ ወይም በአንድ ጊዜ መክፈል ለማይችል ታክስ ከፋይ ሚኒስቴሩ የክፍያ ጊዜ ሊያራዝም እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፤

የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ድጋፍና እገዛ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ፤

ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልበት ጊዜ የተራዘመ የዕዳ መክፈያ ጊዜ ስምምነት በማስገባትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚስተናገድበትን ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ስለሆነ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 32(2) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 142/2011"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

1) **"የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ"** ማለት ማንኛውም ታክስ ከፋይ በአዋጁ መሰረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ወይም በወቅቱ ያልተከፈለ የታክስ ዕዳን ለመክፈል ጊዜ እንዲራዘምለት ሲያመለክት በታክስ ህጎች ከተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውጭ እንዲከፈል የሚሰጥ የክፍያ ጊዜ ነው፡፡
2) **"የክፍያ ጊዜ ስምምነት"** ማለት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል ሳይችል ሲቀር ታክስ ከፋዩ እና የታክስ ባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ክፍያው የሚፈጸምበትን ጊዜ እና ሁኔታ በተመለከተ በፅሁፍ የሚያደርጉት ስምምነት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የመዝገብትና ዶኩመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No 1

3) **"የታክስ ከፋዮች ምደባ"** ማለት የታክስ ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በሚያወጣው መስፈርት የከፍተኛ፣ የመካከለኛ፣ የአነስተኛ እና የጥቃቅን ደረጃ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱበት ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያመላክት ነው፡፡

4) **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግደው የማይችል በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰት ማለትም በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ በንግድ ስራ ላይ ጫና የሚፈጥሩ (እንደ ዝርፊያ፣ ጐርፍ፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች) ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም በታክስ ከፋዩ ጽኑ ህመም ወይም ሞት ምክናያት ታክስ ከፋዩ ያለበትን የታክስ ዕዳ መክፈል እንዳይችል የሚያደርግ ምክንያት ማለት ነው፡፡

5) **"ጽኑ ህመም"** ማለት የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ የሌለውግለሰብ ታክስ ከፋይን በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ እንዳይሰራ የሚያደርግና ታክስ ከፋዩ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ ወይም አስታውቆ መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ በታወቀ የህክምና ተቋም ቢያንስ ለአንድ ወር የሚያስተኛ ወይም መንቀሳቀስ በሚያግድ ህመም ላይ መሆኑ በህክምና ማስረጃ የሚረጋገጥ እክል ነው፡፡

6) **"የታክስ ዕዳ"** ማለት እንደአገባቡ በታክስ ህጎች መሰረት በመክፈያ ጊዜው መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ ታክስ እና ወለድ እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጫዎችን ይጨምራል፡፡

7) **"ዋስትና"** ማለት የታክስ ክፍያ ጊዜ እንዲራዘምለት የጠየቀ ታክስ ከፋይ የታክስ ግዴታውን በዉሉ መሰረት ስለመወጣቱ የታክስ ባለስልጣኑ ስጋት ያደረበት እንደሆነ ወይም ሀብቱ ከታገደ በኂላ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድለት ሲሆን በታገደ ሀብት ላይ የተሰጠ ዕግድ ለማንሳት የሚጠየቀው የባንክ ዋስትና ነው፡፡

8) **"የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት"** ማለት በታክስ አስተዳደር ቅጣት አነሳስ መመሪያ መሠረት እንዲነሳ ያልተፈቀደው እና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነቱ አካል የሆነው ተከፋይ አስተዳደራዊ ቅጣት ነው፡፡

9) **"ከፍተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት ታክስ ከፋዩ በግብር ወይም ስለታክስ ዘመኑ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት በልዩ ጥንቃቄ እንዲታይ ወይም ለታክስ ኦዲት ስራ መመረጥ ያለበት መሆኑን የሚያሳይ የተለየ የሥጋት ደረጃ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No 1

10)**"ያልተከፈለ ታክስ"** ማለት በመክፈያ ቀን ወይም የታክስ ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 32 የተመለከተውን የታክስ መክፈያ ጊዜ ያራዘመ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ ቀሪ ታክስ ማለት ነው፡፡

11)**"የታክስ ጊዜ"** ማለት በታክስ አዋጅ መሰረት የታክስ ማስታወቂያ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ነው፡፡

12) **"የታክስ ስሌት*** ማለት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ፣በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት፣ የስጋት ታክስ ስሌት፣ የተሻሻለ ታክስ ስሌት፣ አስተዳደራዊ ቅጣት ፣ ወለድ ወይም በታክስ ህግ መሰረት የሚደረግ ማንኛውም ስሌት ነው፡፡

13) **"አዋጅ "**ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

14) **"ሚኒስቴር"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን የሚኒስቴሩን ቅ/ጽ/ቤት ይጨምራል፡፡

15) **"ባለስልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ናቸው፡፡

16) **"የታክስ ባለስልጣን" ማለት** የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ናቸው፡፡

17) በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ፣ደንብ እንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ለታክስ ባለስልጣኑ በወቅቱ መክፈል ያለበትን ታክስ ወይም የመክፈያ ጊዜው ያለፈበትን ያልተከፈለ ታክስ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችልና የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ በሚጠይቅ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቀድባቸው ወይም ስለሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

### 4. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የሚፈቀደው ፡-

(ሀ) ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳውን በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል ሲሆን፣

(ለ) ታክስ ከፋዩ በታክስ ማስታወቂያ ወይም የታክስ ስሌት ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ዉስጥ የማይገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

2) በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ የተለየ ፣ ሀብት በዕዳ የተያዘበት ወይም ንብረት እንዲሸጥ ጨረታ የወጣበት ታክስ ከፋይ ዕዳውን ለመክፈል ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

### 5. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች፤-

1) የጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ) በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ መክፈል ያለበት የታክስ ዕዳ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበት ሲሆን፤

(ለ) ታክስ ከፋዩ አስቀድሞ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይኖር ዕዳውን ያልከፈለ ሆኖ ሲገኝ፤

(ሐ) የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበት የታክስ ዕዳ መጠን እንደ ታክስ ከፋዩ አመዳደብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ከተቀመጠው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ ፤

2) ታክስ ከፋዩ፡

(ሀ) በታክስ ዘመኑ በከፍተኛ የሥጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ፣

(ለ) ለዕዳው ማስከፈያ ሀብት እና ንብረት የተያዘበት ከሆነ፣

(ሐ) በዕዳው የተያዘበትን ንብረት ለመሸጥ የጨረታ ማስታወቂያ የወጣበት ከሆነ፣

የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚሰጠው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

## 6. ለታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ መልስ ስለመስጠት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 መሰረት በቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ ላይ የታክስ ባለሥልጣኑ የሰጠውን ውሳኔ የሚገልፅ የጽሁፍ ማስታወቂያ ማመልከቻው በቀረበ በ 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ስለሚፈቅደው አካል፣ የመክፈያ ጊዜና አከፋፈሉ

## 7. የክፍያ ጊዜ ስምምነትን ስለሚፈቅደው አካል እና የጊዜ ገደብ ስለመወሰን፣

1) ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ራሱ አስታውቆ የሚከፍለውን የንግድ ትርፍ ግብር መክፈል አለመቻሉን ጠቅሶ ሲያመለክት ጥያቄውን የቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ አሳማኝ ምክንያት መሆኑን ሲያረጋግጥ ከ 3 ወር ሳልበለጠ ጊዜ እንዲራዘምለት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2) በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለ 3 የግብር ዘመን ተመሳሳይ ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ የታክስ ዕዳ መክፈያ ጊዜ አይራዘምለትም፡፡

## 8. የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስለመወሰን

ታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ደርሶት በዚህ መመሪያ መሰረት የታክስ ክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ ስምምነት ውል ሲገባ የዕዳው የመክፈያ ጊዜ የሚወሰነው በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡፡

1) በከፍተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-
   - (ሀ) ከብር 750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ/ እስከ 2,500,000/ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ህ/ ከሆነ እስከ 6 ወር፣
   - (ለ) ከብር 2,500,001/ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ. አንድ / እስከ ብር 3,750,000 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ/ ከሆነ እስከ 8 ወር፣

Ethiopian Min... Records & Doc... No 1

(ሐ) ከብር 3,750,001 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ. አንድ/ እስከ 5,000,000/ አምስት ሚሊዮን/ከሆነ እስከ 10 ወር፣

(መ) ከብር 5,000,000/አምስት ሚሊዮን/ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

2) በመካከለኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 50,000 /ሀምሳ ሺ. / እስከ ብር 125,000/አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺ/ከሆነ 3 ወር፣

(ለ) ከብር 125,001/አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺ. አንድ/ እስከ 750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ./ ከሆነ እስከ 6 ወር፣

(ሐ) ከብር 750,001 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ. አንድ/ እስከ 2,500,000/ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ./ ከሆነ እስከ 8 ወር፣

(መ) ከብር 2,500,000/ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ. አንድ/ እስከ ብር 3,750,000 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ./ ከሆነ እስከ 10 ወር፣

(ሠ) ከብር 3,750,000 /ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ./ በላይ ከሆነ 12 ወር፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።

3) በአነስተኛ ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና የወለድ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 5,000/አምስት ሺ./ እስከ 12,500 /አስራ ሁለት ሺ. አምስት መቶ/ ከሆነ እስከ 3 ወር፣

(ለ) ከብር 12,501 /አስራ ሁለት ሺ. አምስት መቶ አንድ/ እስከ ብር 75,000 /ሰባ አምስት ሺ.ህ/ ከሆነ እስከ 6 ወር፣

(ሐ) ከብር 75,001 /ሰባ አምስት ሺ. አንድ/ እስከ ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ./ ከሆነ እስከ 8 ወር፣

(መ) ከብር 250,001 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ. አንድ/ እስከ 750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ/ ከሆነ እስከ 10 ወር፤



የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & D... No 1

(ሠ) ከብር 750,000 /ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ/ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) በጥቃቅን ታክስ ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለግበት ጠቅላላ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ዕዳ፡-

(ሀ) ከብር 1000 (አንድ ሺ.) እስከ 10,000 (አስር ሺ.) ከሆነ እስከ 3 ወር፣

(ለ) ከብር 10,001(አስር ሺ. አንድ) እስከ 20,000 (ሃያ ሺ.) ከሆነ እስከ 6 ወር፣

(ሐ) ከብር 20,001(ሀያ ሺ. አንድ) እስከ 40,000 (አርባ ሺ.) ከሆነ እስከ 8 ወር፣

(መ) ከብር 40,001(አርባ ሺ. አንድ) እስከ 60,000 (ስልሳ ሺ.) ከሆነ እስከ 10 ወር፣

(ሠ) ከብር 60,001 (ስልሳ ሺ.) በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር፣

የክፍያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተመለከቱት በየክልሉ ከተጨባጭ ሁኔታዎች ተመስርቶ በተለየ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላቱ ተረጋግጦ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ከታክስ ባለስልጣኑ ጋር የክፍያ ጊዜ ስምምነት እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በተገለጸው መሠረት የታክስ ዕዳ ዋና ታክስ፣ ወለድ፣ መቀጫ ያካተተ ከሆነ በአስተዳደራዊ መቀጫ አነሳስ መመሪያ መሠረት የማይነሳው መቀጫ መጠን ብቻ ተሰልቶ የውሉ አካል የሚደረግ ሲሆን፣ መቀጫው የሚነሳው በውሉ ውስጥ የተካተተው ዋና ታክስ፣ ወለድና የማይነሳ መቀጫ እንደሚከፈል ከተረጋገጠ በኋላ ይሆናል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 መሰረት ታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ተፈራርሞ ግዴታውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻለ ሆኖ በድጋሚ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጠው ከማስረጃ ጋር ጥያቄውን ሲያቀርብ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ስራ ሂደት አስተባባሪ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ስራ/አስኪያጅ በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት የቀረበለት የስራ ሀላፊ ማስረጃውን በመመዘን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 በተመለከተው የመክፈያ ጊዜ አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት ዕዳውን እንዲከፍል በድጋሚ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ሆኖም ግን

ድጋሚ ተፈቅዶለት ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ ሌላ የታክስ ማራዘሚያ ስምምነት ሊፈቀድለት አይቻልም።

## ክፍል አራት
## የማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ፣ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና የአፈፃፀም ሥርዓቱ

### 9. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ እንዲፈቀድለት የሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ፣-

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት በሚገባባቸው የታክስ ዕዳዎች ቢያንስ 25% ቅድሚያ ክፍያ መክፈል አለበት።
2) የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ የቀረበው የታክስ ከፋዩ ሀብት ከተያዘ በኋላ ሲሆን የታክስ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን ለማስፈጸም ያወጣቸውን ወጪዎችን እና ቢያንስ የታክስ ዕዳውን 25% ቅድሚያ ክፍያ መክፈል አለበት።
3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን ለማስፈፀም ለታክስ ዕዳ ሀብት የተያዘበት የታክስ ከፋይ ዕገዳው ሊነሳለት የሚችለው ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ የባንክ ዋስትና ሲያቀርብ ብቻ ነው።
4) ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሱትን ቅድሚያ ክፍያ ለመወሰን የስሌት መሠረቱ ዋና ታክስ ፣ ወለድና የማይነሳው መቀጫ መጠን ይሆናል።
5) ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የታክስ ባለሥልጣኑ የታክስ ዕዳ አሰባሰቡን ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ጋር በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል።
6) የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በውሳኔው ላይ ባለመስማማት ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የስራ ክፍል ቅሬታውን ሲያቀርብ አምኖ የከፈለው ታክስ ወይም ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቅሬታውን ሲያቀርብ የከፈለው ታክስ የመክፈያ ጊዜ ስምምነት በሚገባበት ጊዜ ለቅድሚያ ክፍያው እና ለቀሪ ዕዳው ተቀናሽ ይደረግለታል።
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን እና በመክፈያ ጊዜ የሚፈጸመው የአከፋፈሉ ቅደም ተከተልም በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 34 መሰረት ይሆናል።

8) ቅድሚያ ክፍያ ከተፈጸመ በኋላ ላሉት ቀሪ ክፍያዎች የመክፈያ ጊዜው የሚታሰበው ቅድሚያ ክፍያው ከተፈጸመበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን ነው።

9) በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገባበት የታክስ ክፍያ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው ስሌት መሠረት ወለድ ይከፈልበታል።

10) በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን በታክስ ክፍዩ ካልተከፈለው ዋና ታክስ ሊበልጥ አይችልም።

11) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 አፈፃፀም ወለድ የሚታሰበው ባልተከፈለው ወይም በሚቀረው ጠቅላላ ዋና ታክስ ላይ ብቻ ነው።

12) የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ ወይም ታክሱን የክፍያ ጊዜ ስምምነት ገብቶ በመክፈል ላይ ያለ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 105 መሰረት ታክስን አዘግይቶ መክፈል የሚያስከትለው ቅጣት አይታሰብበትም።

## 10. <u>በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 7፣ 8 እና 9 ላይ የተመለከተው ቢኖርም በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

2) በልዩ ሁኔታ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚቀርቡት ለቅ/ጽ/ቤቱ ይሆናል።

3) ቅ/ጽቤቱ ስለ ታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክና በልዩ ሁኔታ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተጠየቀበትን ምክንያት አጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ይልካል።

4) የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬቱ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ ወይም ለወከለው የስራ ኃላፊ አቅርቦ በሚወሰነው መሰረት እንዲፈፀም ለቅ/ጽቤቱ መልሶ ያስተላልፋል።

5) ሚኒስትሩ ወይም በእርሳቸው የተወከለው የስራ ሀላፊ የክፍያ ስምምነት ለገባ ታክስ ከፋይ ያለበትን የእዳ ጫና ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅድሚያ ክፍያውን እስከ 15 በመቶ ዝቅ ሊያደርግ ይችላል።

6) የአዲስ አበባና ድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣንን በተመለከተ በተመሳሳይ ደረጃ ባሉ ሀላፊዎች ይከናወናል።

## 11. የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ፣ ስለሚፈቅደው አካል እና አፈፃፀም ሥርዓት

1) የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በአንዴ የመክፈል አቅም የሌለው መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ለቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ስራ ሂደት ሲያቀርብ እና ምክንያቱ ተቀባይነት ሲያገኝ በዚህ መመሪያ በተገለፀው ሁኔታ የሚስተናገድ ይሆናል።
2) ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከሆነ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ስራ ሂደት አስተባባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ባለው መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ሊፈቅድ ይችላል።
3) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት በድጋሚ የቀረበ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ከሆነ የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚፈቅድ ይሆናል።
4) በአንቀጽ 7(1)፣በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 እንዲሁም በአንቀጽ 10 መሠረት ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በቅ/ጽ/ቤቱ ለሥራው አግባብነት ያለው የታክስ ዕዳ አስተዳደር ባለሙያ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ለሥራ ሂደት መሪው አቅርቦ እንዲፈረም ያደርጋል።
5) የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ 3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል፣ 2ኛው ኮፒ ለግብር ከፋዩ ይሰጣል፣ 3ኛው ኮፒ በታክስ ዕዳ ክትትል ስራ ሂደት ለቀጣይ የክትትል ስራ የሚያዝ ይሆናል።
6) በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውሉ መሠረት ክፍያ የሚፈጸምበት ቀን በበዓላት ወይም በእረፍት ቀናት ላይ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን ይሆናል።
7) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የጳጉሜ ወር የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል።
8) የታክስ ዕዳ ክትትል የሥራ ሂደት አስተባባሪ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የገቡ ታክስ ከፋዮች የክፍያ ስምምነት የተገባበትን የታክስ ዓይነት፣ የታክስ ዘመን፣ ዋና ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ መጠን፣ ስምምነት የተገባበት ቀን እና የመክፈያ ጊዜ ያካተተ ዝርዝር መረጃ ሪፖርት በየወሩ እያዘጋጀ ለዋና መ/ቤት ለታክስ እዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ይልካል።

## 12. የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ግዴታን አለመፈጸም

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በውሉ መሠረት በየወሩ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ካቆመበት ጊዜ አንስቶ ያልተከፈለዉን ቀሪ ክፍያ እና ቀሪ መቀጫ ተሰልቶ በሙሉ እንዲከፍል በታክስ ባለሥልጣኑ የዕዳ አሰባሰብ የስራ ክፍል በታክስ ህጉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ክፍያ ያቋረጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ አቋርጦት የነበረውን ታክስ በስምምነት ውል ጊዜ ውስጥ ያልከፈለውን ወራት አጠቃሎ እና የወጡ ወጪዎችን ጨምሮ የከፈለ ከሆነ የስምምነቱ ውል ሳይሰረዝ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

### ክፍል አምስት
### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 13. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ስራ ላይ በነበረዉ መመሪያ ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ተፈቅዶ በስምምነት ውሉ መሰረት በመከፈል ላይ ያለ የታክስ ዕዳ በነበረው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

## 14. ስለተሻሩ መመሪያዎች

በመመሪያ ቁጥር 55/2003 ስለ ታክስ ክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገለጹ አንቀጾች እና በተለያየ ጊዜ ለአፈጻጸም የተላለፉ ሰርኩላሮች በዚህ መመሪያ የተተኩ ስለሆነ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 15. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
2011 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር